የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

አሥራአምስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፪
አዲስ አበባ ሚያዝያ ፳፰ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No. 32
ADDIS ABABA 6th May, 2009

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፭/፪ሺ፩ ዓ.ም

ለኢትዮ-ጂቡቲ የኃይል ትስስር ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ለማግኘት ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ጋር የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ … ገጽ ፬ሺ፯፻፩

**CONTENTS**

**Proclamation No. 625/2009**

The African Development Fund Supplementary Loan Agreement for the Ethio-Djibouti Power Interconnection Project Ratification Proclamation Page 4701

## አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፭/፪ሺ፩

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለኢትዮ-ጂቡቲ የኃይል ትስስር ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ፭ሚሊዮን፪፻ሺ ዩኒትስ ኦፍ አካውንት /አምስት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺ ዩኒ ትስ ኦፍ አካውንት/ የሆነ ተጨማሪ ገንዘብ የሚያስ ገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ኖቬምበር ፲፫ ቀን ፪ሺ፰ የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራ ላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዝያ ፲፫ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለኢትዮ-ጂቡቲ የኃይል ትስስር ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ለማግኘት ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ጋር የተፈረ መው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፭/፪ሺ፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 625/2009

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE AFRICAN DEVELOPMENT FUND

**WHEREAS,** a Loan Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund stipulating that the African Development Fund provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia supplementary loan in an amount not exceeding 5,200,000 UA (five million two hundred thousand Units of Account) for financing the Ethio-Djibouti Power Interconnection Project was signed on the 13th day of November 2008;

**WHEREAS,** the House of peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 21st day of April, 2009;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "The African Development Fund Supplementary Loan Agreement for the Ethio-Djibouti Power Interconnection Project Ratification Proclamation No. 625/2009".

## ፪. <u>የስምምነቱ መጽደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ኖቬምበር ፲፫ ቀን ፪ሺ፰ የተፈረመው ቁጥር 2100150017643 የብድር ስምምነት ፀድቋል።

## ፫. <u>የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፭ሚሊዮን፪፻ሺ ዩኒትስ ኦፍ አካውንት /አምስት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺ ዩኒትስ ኦፍ አካውንት/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሚያዝያ ፳፰ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 2. <u>Ratification of the Agreement</u>

The Loan Agreement No. 2100150017643 signed on the 13th day of November 2008 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund is hereby ratified.

## 3. <u>Power of the Ministry of Finance and Economic Development</u>

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of 5,200,000 UA (five million two hundred thousand Units of Account) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

## 4. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 6th day of May, 2009**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**